የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄን
Ginbot 7: Movement for Justice Freedom and Democracy
Tel +44  208 1335670        pr@ginbot7.org

ቀን ታህሣሥ 21 2001

# በአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር በወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የወሰደውን የእብሪት እርምጃ አስመልክቶ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ።

በትናንትናው እለት ታህሳስ 20 2001 ኢ.ም የመለስ ዜናዊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የወሰደውን በእብሪት የተሞላ የእስራት እርምጃና በ78 አመቱ አረጋዊ በእውቁ የሰብአዊ መብት ተሚጋች በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ላይ የተፈጸመውን ድብደባ የግንቦት 7 ንቅናቄ አጥብቆ ያወግዛል። በእዚህ አጋጣሚ የእብሪት አገዛዙ በቅርቡ በወይዘሮ መሰበ-ወርቅ ቅጣው የመኢአድ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ፣ በአቶ በቀለ ጅራታ የኦፍዴን ዋና ጸሃፊና እንዲሁም በሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት ላይ የወሰደውን ተመሳሳይ የአፈና እርምጃ የግንቦት 7 ንቅናቄ አጥብቆ ይኮንናል። ከእዚህ በተጨማሪ አገዛዙ የተለያዩ ድርጅቶችን አባላትንና ደጋፊዎችን ማንገላታትና ማፈኑን፣ ዜጎችን በዘራቸው እየለየ በጅምላ ማሰሩን፣ ማሰቃየቱንና የግድያ እርምጃ መውሰዱን የግንቦት 7 ንቅናቄ አምርሮ ይኮንናል።

ንቅናቄያችን በተለያዩ ወቅቶች የመለስ አገዛዝ የሚፈጽመውን የግፍ ድርጊት የሚኮንኑ መግለጫዎችን ማውጣቱ ቢታወስም የወይዘሪት ብርቱካንን በግፍ መታሰር ምክንያት በማድርግ ይህንን መግለጫ ለማውጣት የተገደደበት የራሱ ምክንያት አለው። ከግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር አካላት መሃል የተወሰኑቱ እንደ ወ/ት ብርቱካን በቅንጅት መሪነታቸው በግፍ የተከሰሱ፣ የታሰሩና እንደ ወ/ት ብርተካን እንዴት ከእስር እንደተፈቱ ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው፣ የአንድነት  ፓርቲ ሊቀመንበሯ ይህንን ከእስር የመፈታት ሂደት በሚመለከት የሰጡት የቃልም ይሁን የጽሁፍ መግለጫ አንዱም ስንኝ ሳይቀር በወቅቱ የሆነውን ሃቅ የሚያንጸባርቅ ትክክለኛ አቋም መሆኑን የምስክርነት ቃል ለመስጠት ነው። የወ/ት ብርቱካን መግለጫ እንኳን በሃሰት ክስ ላይ የተመሰረተንና በይቅር እንባባል መንፈስ የተሰረዘን ፍርደ-ገምድላዊ የእድሜ ልክ እስራት የሚያስጀመር ቅጣት ቀርቶ በፖሊስ አስጠርቶ ሊያስጠይቅ የማይገባው ጉዳይ እንደሆነ የግንቦት 7 ንቅናቄ ማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ ማሳወቅ ይወዳል።

ይህ በትናንትናው እለት በወ/ት ብርቱካንና ከዚያም በፊት በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት ላይ የተወሰደው የእብሪት እርምጃ ያነጣጠረው በሃገራችን ውስጥ ለዴሞክራሲ መከበር ትግላቸውን ህግንና ሰላምን አጥብቀው  በመያዝ የሚያደርጉትን አካላት እንቅስቃሴ ሲቻል ለመግደል፣ ባይቻል ለማዳከም በመለስ አገዛዝ ሆነ ተብሎ በስራ ላይ እየዋለ ያለ ፖሊሲ መሆኑን ሁሉም ሊያውቀው ይገባል። እንዲህ አይነቱ የስርአቱ የእብሪት እርምጃ ጾታን፣ እድሜን፣ ዘርንና ሃይማኖትን ሳይለይ በሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች ላይ እየደረሰ ያለ በደል መሆኑን በመረዳት፣ ይህንን ማስቆም የሚቻለው ሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች በጋራ ሲኮንኑትና አገዛዙን በጋራ ሊታገሉት ሲችሉ ነው ብሎ የግንቦት 7 ንቅናቄ ያምናል።

በእዚህ አጋጣሚ ለዴሞክራሲያዊና ለሰብአዊ መብት መከበር ቆመናል የሚሉ መንግስታትና የሰብአዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች፣ ይህ በሃገራችን እየተፈጸመ ያለው የውንብድና እርምጃ እንዲቆም ለማድረግ የሚቻላቸውን እርምጃ በሙሉ እንዲወስዱ የግንቦት 7 ንቅናቄ ጥሪውን ያቀርባል። በእዚህ ፈታኝ ወቅትም በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ የሚገኘው የሃገሪቱ ዜጋ በሙሉ በመለስ አገዛዝ ለሚሰቃዩ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች አባላትና ሌላም ዜጋ በሙሉ የትግል አጋርነቱን በሚቻለው መንገድ ሁሉ እንዲያሳይ ወገናዊ ጨሁኸቱን ግንቦት 7 ያደርሳል።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ
የግንቦት 7 የፍትሕ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
www.ginbot7.org